Ethiolion

# በተፈጥሮ ሀብትሽ ፣ ነግሷል ድህነትሽ

የባዕድ ጆሮ ጠቢ - ሰባቂ ምንደኛ

መሪሽ እንደራሴው - ምሁርሽ ቅጥረኛ

የሶስተኛው ዓለም - በተለይ አፍሪቃ

የድንቁርናን ጌጥ - የድህነት ጾቃ

የግፍ ቀንበር ገዝቶ - በሀብትሽ ሰቆቃ

ዩራኒየም ኮባልት - አልማዝና ብሩ

የወርቅሽ ማዕድን - ዘይተሽ አፈሩ

የውሃ ፍሳሽ ሀብትሽ - ወንዝሽ ሸንተረሩ

ወይ አቀማመጥሽ - ከነመልክዓ ምድሩ

ወይ የህዝብሽ ብዛት - ፈጣን ዕድገት ቁጥሩ

እያለሽ የሌለሽ - ድሃ ሀብት አፍላቂ

ርሃብ የፈታው - የሞት ስንቅ ሰናቂ

ሀብትሽ ነው ያረገሽ - በራስሽ አላቂ ።

ሀብትሽ በእጅሽ ይሁን - መመዝበርሽ ይብቃ

ህዝብሽ ከምኝታው - ተቀስቅሶ ይንቃ

ከአልጀሪያ እስከ ጁባ - ከቻድ እስከ አንጎላ

ከኒዠር ሞዛምቢክ - አቢሲኒያ አዶላ

አመፅ ነው መፍትሄው - ጥቁሩ ደም ሲቀላ

ለዓለም ይሁን ይፋ - በነጋሪት አዋጅ

ቀንበርሽ ይሰበር - ምድሩም በደም ይዋጅ።

ግንቦት 2002

abraham beyenne

EthioLion.com

Ethiopia Will Prevail!